# የኮንቬንሽንናል ቢንጎ ጨዋታ ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 126/2013

Conventional Bingo Game
Licensing and Control Directive No. 126/2013

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority

የካቲት 1÷ 2002

## *የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር* **126/2013**

ኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ በሀገራችን ውስጥ ባሉ ትልልቅ ከተሞች እየተዘወተረ የሚገኝ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ ሲሆን፣ ሕብረተሰቡ የዕረፍት ጊዜውን በአስፈላጊው ቦታና ጊዜ እየተዝናና እንዲያሳልፍ ለማስቻል ጨዋታውን በህግና በሥርዓት መምራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ጨዋታውን በህግና በሥርዓት ከመምራት ጎን ለጎን ጨዋታው የሚካሄድበትን ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ መወሰን በማስፈለጉና ከጨዋታውም የመንግሥትን የልማት ጥረት የሚያግዝ ገቢ እንደሚገኝ በመታመኑ፤

ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 21 መሠረት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "ተሻሽሎ የወጣ የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር. ***126/2013***" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. *ትርጓሜ*

በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

2.1. "ባለስልጣን" እና "ዋና ዳይሬክተር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፤

2.2. "አስተዳደር" ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው፡፡

2.3. "የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ" ማለት ተጫዋቹ በቢንጎ ማጫወቻ ቦታ በመገኘትና በቅድሚያ ካርድ በመግዛት ከአጫዋቹ የሚሰጡ ትዕዛዞችን ከማሳያ ማሽኑና ከራሱ የመጫወቻ ካርድ ቁጥሮች ጋር እያመሳከረ አሸናፊ መሆን አለመሆኑ የሚታወቅበት እና ሽልማቱ በገንዘብ የሚሰጥበት የጨዋታ ዓይነት ነው፤

2.4. «ሰው» ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

2.5. "ፈቃድ" ማለት ዕጣን ወይም ዕድልን መሠረት ያደረገ የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ በማካሄድ ከጨዋታው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ ለጋራ ዓላማ ማዋል ለሚችሉ ማህበሮች፣ ክበቦች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ከተጣራ ገቢያቸው 51% ለማህበራዊ ዓላማ ለማዋል ለሚስማሙ ግለሰቦች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

2.6 "ክፍያ " ማለት አዲስ ፈቃድ ከመሰጠት፣ ከፈቃድ ዕድሳትና ከኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ከሚሰበሰብ ጠቅላላ ገቢ ላይ የጨዋታው አሸናፊዎች ሽልማት ተቀንሶ

አንቀጽ 1 በፊደል (ሐ) መሠረት አስተዳደሩ ከባለ ፈቃዱ የሚሰበሰበው ነው፡

## 3. *የፈቃድ አስፈላጊነት*

በአስተዳደሩ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ማናቸውንም የሎተሪ ሥራ ማካሄድ ስለማይችል ማንኛውም የቢንጎ ሎተሪ ጨዋታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው አስተዳደሩ የሚሰጠውን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

## 4. *የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ*

4.1. የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ለማካሄድ ፈቃድ እንዲሰጠው የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻውን በጽሑፍ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት፣

4.2. ፈቃድ ጠያቂው የሚያቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፣

4.2.1. የፈቃድ ጠያቂው ሰው ስምና ሙሉ አድራሻ፤

4.2.2. የቢንጎ ጨዋታ ስለሚካሄድበት ቦታና ጊዜ፤

4.2.3. ስለመጫወቻ መሣሪያውና የመጫወቻ ቦታው የባለቤትነት ሁኔታ /ይዞታ/፤

4.2.4. ሥራውን ለማካሄድ ቢያንስ 100 ሰው ሊይዝ የሚችል ንፁህና ፅዱ የማጫወቻ ቦታ ከበቂ የመፀዳጃ ቤት ጋር ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

4.2.5. የማጫወቻ ቦታው ለመዝናኛ የሚሆኑ የተሟሉ አቅርቦቶች ያሉት ስለመሆኑ፤

4.2.6. ስለመጫወቻ ቦታው የፀጥታ ጥበቃ ሁኔታ፤

4.2.7. ስለቢንጎ ኳስ ማውጫ መሣሪያው እና የመጫወቻ ካርዱ ዓይነትና መሣሪያው ስለተመረተበት /ስለሚገዛበት/ አገር/፤

4.2.8. በዕቅድ ደረጃ በሥራው ሊያሠማራ ያሰበውን የሰው ኃይል ብዛትና የሙያ ስብጥር፤

4.2.9. ገለልተኛ የሆኑ ጨዋታውን የሚመሩ የአጫዋቾች ስምና አድራሻ፤

4.2.10. ከጨዋታው ስለሚገኝ የተጣራ ገቢ አጠቃቀም፤

4.2.11. ጨዋታው የሚመራበትን ደንብ፤

## 5. *ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታና በፈቃድ ጠያቂው በቅድሚያ ሊታወቁ ስለሚገባቸው ግዴታዎች*

5.1. አስተዳደሩ አመልካቾች ያቀረቧቸውን መረጃዎችና ማስረጃዎች በመመርመር የተሟሉና አሳማኝ ሆነው ሲያገኛቸው ሌሎች በአስተዳደሩ የሚፈለጉ ግዴታዎችና ክፍያዎች እንዲፈፀሙ በማድረግ ፈቃድ ይሰጣል፣

5.2. ከአስተዳደሩ ፈቃድ የወሰደ ሰው፡-

5.2.1. ለአንድ ጨዋታ የተዘጋጀ የቢንጎ ካርድ ሳያልቅ ለሌላ ዙር ጨዋታ የተዘጋጀን የቢንጎ ካርድ ደርቦ ያለመሸጥ፤

5.2.2. ጨዋታው የሚካሄድባቸው የመሣሪያ አይነቶች ተገቢውን መስፈርት የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

ለተጨዋቾቹ የመግለጽ፤

5.2.4. የኳሶቹን ክብደት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ እንዲሁም የኳሶቹን ዙር ለማዛባት ምንም ዓይነት ባዕድ ነገር ያለመጠቀም፤

5.2.5. በጨዋታ ቦታው ወንጀል እንዳይፈፀም እና የቁማር ጨዋታዎች እንዳይካሄዱ በኃላፊነት የመከላከል፤

5.2.6. የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የገቢና የወጪ መዝገብ መያዝና ለምርመራ ለአስተዳደሩ ተቆጣጣሪዎች በተጠየቀ ጊዜ የማቅረብ፤

5.2.7. የማሳያ ማሽኑን ለጨዋታው ተሳታፊዎች ግልፅ ሆኖ ሊታይ በሚችልበት ቦታ የማስቀመጥ፤

5.2.8. በቢንጎ ካርዱ ላይ ሌላ ዓይነት አነስተኛ የቁማር ጨዋታዎች እንዳይካሄዱ የመከልከልና የመቆጣጠር ፤

5.2.9. ለቢንጎ አሸናፊው ወዲያውኑ ክፍያ የመፈፀም፤

5.2.10. በጨዋታው ወቅት የድምፅ ማጉያ መሣሪያዎች የተስተካከሉና በጥራት የሚያሰሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

5.2.11. ለአሸናፊው ሽልማቱን ታዛቢዎች በሚገኙበት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.3 የተገለፀውን ተቀናሽ በማድረግ ወዲያውኑ የመፈፀም ግዴታ አለበት።

6. <u>*ስለፈቃድና ሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎች*</u>

6.1. የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ባለፈቃድ አዲስ ፈቃድ ሲያወጣ ብር 400.00 (አራት መቶ ብር) ፣ ለአመታዊ የፈቃድ ዕድሳት ደግሞ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ክፍያ ይፈጽማል፡

6.2. ለመንግሥት የሚከፈለው ግብር እንደተጠበቀ ሆኖ ከኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ከሚሰበሰብ ጠቅላላ ገቢ ለቢንጎ አሸናፊዎች የሚፈጸመው ሽልማት ብቻ ተቀንሶ በቀሪው ላይ 15% ታስቦ ወሩ በገባ እስከ አስራ አምስተኛው ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ የኮሚሽን ክፍያ መፈፀም አለበት።

6.3. ከብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በላይ አሸናፊ ስሆነ የቢንጎ ተጨዋች በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት ከብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በላይ ስሆነው ብቻ የ15% የገቢ ግብር በባለፈቃዱ ድርጅት አማካኝነት ተሰብስቦ ለግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት በየወሩ ገቢ ይደረጋል፤

7. <u>*ወርሃዊ የክፍያ ግዴታን አዘግይቶ በመክፈል የሚጣል መቀጫ*</u>

ማናቸውም የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታን ለማጫወት ፈቃድ የወሰደ በየወሩ ለአስተዳደሩ መፈፀም ያለበትን ክፍያ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያልከፈለ እንደሆነ የሚከተለው መቀጫ ይጣልበታል።

C:\Documents and Settings\Administrator\My Documents\Bingo Revised Directive 2002.doc

7.1. ወርሃዊ ክፍያው ሊፈፀም ከሚገባው የመጨረሻ ቀን ካለፈ ክፍያው 20% መቀጫ ጨምሮ ከሚቀጥለው ወር ክፍያ ጋር እንዲፈፀም ይደረጋል፣

7.2. ክፍያው ለሁለት ተከታታይ ወራት ሳይፈፀም ከቀረ የሁለቱ ወራት ክፍያ 50% መቀጫን ጨምሮ ከሶስተኛው ወር ክፍያ ጋር እንዲፈፀም ይደረጋል፣

7.3. ክፍያው ከሁለት ተከታታይ ወራት በላይ ከዘገየ ከ100% መቀጫ ጋር እንዲፈፀም የሚደረግ ሲሆን፣ ለመፈፀም ፈቃደኛነቱ ከሌለ ባለፈቃዱ በሕግ እንዲጠየቅ ይደረጋል፣

8. *ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ*

8.1. ለአስተዳደሩ የቀረበ የፈቃድ ጥያቄ በመመሪያው አንቀፅ 4 በተገለፀው መሰረት ተሟልቶ ካልቀረበ ፈቃድ አይሰጥም፤

8.2. የቢንጎ ማጫወቻ መሣሪያዎች ዓይነትና ሁኔታ በመመሪያው አንቀፅ 4 ተራ ቁጥር 4.2.7 በተገለፀው መሰረት ካልሆነ ፈቃድ አይሰጥም፤

8.3. በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 12 ከተገለፀው ሁኔታ ውጪ በማንኛውም ሰው የሚቀርብ የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ የፈቃድ ጥያቄ አይስተናገድም፤

9. *የማጫወቻ /የሥራ/ ሰዓትን ስለመወሰን*

9.1. ከሰኞ እስከ አርብ ባሉ የሥራ ቀናት ጨዋታው ከቀኑ 10:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2:30 ይካሄዳል፣

9.2. ቅዳሜ፣ እሁድና በብሔራዊ በዓላት ብቻ ከቀኑ 4:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2:30 ሰዓት ድረስ ይከሄዳል፣

9.3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 9.1 እና 9.2 የተጠቀሰው ቢኖርም ፤ የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታው ሥራ አስኪያጅ የተጫዋቾችን ቁጥርና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከተቀመጠው የመዝጊያ ሰዓት አስቀድሞ ጨዋታው እንዲቆም ሊያደርግ ይችላል፣

10. *ስለጨዋታው ተሳታፊ አካላት*

ማንኛውም ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ ያለ ሰው በጫወታው መሳተፍ ይችላል፣

11. *<u>የተከለከሉ ጉዳዮች</u>*

11.1. የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ በሚካሄድበት ቦታ የሚሠሩ ሠራተኞች የኮንቬንሽናል ቢንጎ እንዲጫወቱ አይፈቀድላቸውም፤

11.2. ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ ወደሚካሄድበት ቦታ መግባትም ሆነ መጫወት አይፈቀድለትም፣

12. *<u>ጨዋታውን የሚያካሂዱ ሰዎችን ስለመወሰን</u>*

ከቢንጎ ጨዋታ የሚገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ የጋራ ማህበራዊ ዓላማን ለማስፈፀም ማለትም ለስፖርት ክለብ፣ ለበጎ አድራጎት ሥራ ወይም የተጣራ ገቢውን 51% ለጋራ ማህበራዊ ዓላማ ወይም በጎ ተግባር ለማዋል የሚስማማና ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ማንኛውም ሰው የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታን ለማካሄድ ፈቃድ ይሰጠዋል።

13. *<u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>*

13.1. አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ /የተመለከቱ/ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

13.2. የአስተዳደሩ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ የተሰጠውን የሥልጣን ማረጋገጫና መታወቂያ ወረቀት ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት ድርጅት ባለቤት ፣ ወኪል ወይም አጫዋች ሠራተኞች በማሳየት በማናቸውም ጨዋታው በሚካሄድበት ቦታና ሰዓት ቁጥጥር ያደርጋል፣

14. *<u>ስለፈቃድ ዕድሳት</u>*

14.1. የኮንቬንሽናል ቢንጎ ጨዋታ የሥራ ፈቃድ በየዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፣

14.2. ፈቃድ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ ዓመት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ አለበት፣

14.3. አመልካች ፈቃዱ እንዲታደስለት ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የዘመኑን የመንግሥት ግብርና ታክስ ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፣

14.4. አስተዳደሩ የአመልካቹን የሥራ ክንውንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከገመገመ በኋላ ማመልከቻው በደረሰው በ8 ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ያድሳል ወይም ፈቃዱ ሊታደስ የማይችል መሆኑን ከነምክንያቱ በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል፣

14.5. ፈቃድ ለማሳደስ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 14.2 በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር) የመቀጫ ክፍያ በመፈፀም የፈቃድ እድሳቱን ያከናውናል፣

15. <u>ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ</u>

15.1. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ይህን መመሪያ ከጣሰ ወይም ከተፈቀደለት ውጭ ከሠራ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እስኪወስድ ድረስ አስተዳደሩ የሰጠውን ፈቃድ ያግዳል፣

15.2. አስተዳደሩ ከዚህ በታች የተገለጹ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ የሰጠውን ፈቃድ ሊሠርዝ ይችላል።

15.2.1. አመልካች ፈቃዱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ /መረጃ/ በማቅረብ ወይም በመስጠት የሆነ እንደሆነ፤

15.2.2. የተሰጠው ፈቃድ በአስተዳደሩ ሳይፈቀድ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ፤

15.2.3. በፈቃዱ የህዝብን ሰላም፣ ፀጥታና የአገሪቱን ደህንነት የሚጎዳ ተግባር ሲሠራበት ወይም የማጭበርበር ድርጊት ሲፈጽምበት ከተገኘ፤

15.2.4. ፈቃዱን ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን ባለው ጊዜ ካላደሰ እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 በንዑስ አንቀጽ 14.5 መሠረት በወቅቱ የፈቃድ እድሳት ባለማድረጉ የተጣለውን መቀጫ ከፍሎ ካላሳደሰ፤

15.2.5. አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6.2 ላይ የተመለከተውን ወርሃዊ የክፍያ ግዴታ በንዑስ አንቀጽ 7.3 መሠረት መቀጫውን መክፈል ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ እንዲሆን፤

15.3. አስተዳደሩ የሰጠውን ፈቃድ ከማገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት የማገዱን ወይም የመሠረዙን እርምጃና እርምጃውን የሚወስድበትን ምክንያት ለባለፈቃዱ በጽሑፍ በመግለጽ፣ ባለፈቃዱ ጽሑፉ በደረሰው በሰባት /7/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ የበኩሉን አስተያየት በጽሑፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፡

15.4. በዚፅ አንቀጽ በንዑስ አንቋፅ 15.3 በተገለፀው መሠረት ባለፈቃዱ መልስ ካልሰጠ ወይም የሰጠው መልስ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ አስተዳደሩ ፈቃዱን ማገድ ወይም መሠረዝ ይችላል፣

16. <u>ስለቅጣት</u>

ድርጊቱ በወንጀል ህግ መሠረት የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በአስተዳደሩ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀፅ 20 መሰረት ፡-

16.1 ማንኛውም ሰው የፀና ፍቃድ ሣይኖረው የሎተሪ ሥራ ካካሄደ ከብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

ህንፃ እንዳይገባ የከለከለ ወይም የቁጥጥር ስራው እንዳይካሄድ በማናቸውም መንገድ ያሰናከለ እንደሆነ ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) እስከ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

17. ***መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ***

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

30 መጋቢ 2002

አዲስ አበባ ---------ቀን 2002 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር